# Takoma Park

## አነስተኛ የማስተር ፕላን ማሻሻያ

## የእቅዱ አላማ




የTakoma Park አናሳ ማስተር ፕላን ማሻሻያ በTakoma Park ከተማ እና Montgomery እቅድ ማውጣት መካከል ያለ የጋራ ጥረት ነው። የWashington Adventist Hospital እና የዩኒቨርሲቲ ካምፓሶችን፣ የErie Centerን (በFlower Avenue እና Erie Avenue መገናኛ ላይ የሚገኘው) እና የባለብዙ ቤተሰብ ባህርያትን፣ ፓርኮችን እና የTakoma Park የማህበረሰብ ማዕከል የሆነውና በMaple እና Lee Avenues የሚገኘውን በማካተት የከተማውን ክፍል ዳግም ከግምት ውስጥ በማስገባት የ2000 Takoma Park ማስተር ፕላንን ክፍሎች እቅዱ አዘምኗል።

የእቅዱ አላማ የሚከተሉትን ጭብጦች እውን ለማድረግ ነው፦

- ለነባር ክፍት ስፍራዎች እና ቦታዎች ከአዳዲስ እና የተሻሻሉ አጠቃቀሞች ጋር ዳግም የታሰበ ማህበረሰብ እንዲሁም ለአተገባበር ተለዋዋጭ እና የገበያ ምላሽ ሰጪ መሳሪያዎች ጋር፤
- የአየር ንብረት ለውጥን በመጋፈጥ የተዘጋጀ ማህበረሰብ፣ ለመላመድ የሚችል፣ ማሻሻያ የሚያደርግ እና የበለጸገ ተቋቁሞ የሚያልፍ ማህበረሰብ፤ እና
- ወደ ፓርኮች፣ ወደ ግብይት እና ወደ ቤት ለመሄድ የተሻሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቁ እና ጋባዥ መንገዶች ጋር ያለ መልሶ የተገናኘ ማህበረሰብ እና የቀድሞ ታሪኩ ጠንካራ የሆነ ስሜት።

## ህብረተሰቡን ማሳተፍ

የማህበረሰብ ተሳትፎ ጥረቶች በፋል 2021 በመጀመር ውጤቶቹ የእቅድ ማውጣት ሂደቱን ለመምራት እና የእቅዱን ምክረ ኃሳቦች ለማስገንዘብ ጥቅም ላይ ውለዋል። በእቅድ አካባቢው ውስጥ በነባር ሁኔታዎች ላይ ያሉ አጫጭር መግለጫዎች፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም የቅድመ ምክረኃሳቦች የTakoma Park ከተማን እና Montgomery County የእቅድ ማውጣት ቦርድን በማካተት ለባለድርሻ አካላት ቀርበዋል።

ሰራተኞች በሜይ 24፣ 2023 ላይ በነበረው የህዝባዊ ስብሰባ ላይ ለTakoma Park የከተማ ካውንስል እንዲሁም በጁን 8፣ 2023 ላይ በነበረው ሳምንታዊ ስብሰባ ለእቅድ ማውጣት ቦርድ በስራ ላይ ያለውን የዕቅዱን ረቂቅ ለግምገማ ያቀረቡ ሲሆን ይህም እንደ ህዝባዊ የችሎት ረቂቅ ተቀባይነት አግኝቷል።




## የህዝባዊ የችሎት ረቂቅ ቁልፍ ምክረ ኃሳቦች

- የመኖሪያ ቤት ክምችት፣ ክፍት ቦታዎች እና የአጠቃቀሞች ድብልቅ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በዘር ብዝሃ የሆነ ማህበረሰብ ፍላጎቶችን የሚገናኙበት ንቁ፣ የድብልቅ ገቢ ማህበረሰብን ማሰብ
- በእቅዱ ዲስትሪክቶች፣ ከእቅድ አካባቢው ባለፈ የከፍተኛ አቅም ትራንዚት፣ በነባር የዱካ አውታር እና በቅርብ የእንቅስቃሴ ማዕከላት ውስጥ እና መካከል ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ጤናማ እና ምቹ ግንኙነትን ማስተዋወቅ
- የአየር ንብረት ለውጥን ተጽዕኖ ለመቅረፍ የአየር ንብረት-ወደፊት እቅድ እና ዲዛይን ማካተት።
- በፕላኑ አካባቢ አረንጓዴ፣ ቀልጣፋ እና ማራኪ የእግረኞች ግንኙነት ለማቅረብ የመራመጃ መንገድን መተግበር።
- ታሪካዊ ግብአቶችን መጠበቅ እና ልዩ የሆነ የቦታ ስሜትን ለማስተዋወቅ የማህበረሰብ ታሪክን አተረጓጎም ማቅረብ።

እቅዱ ከነባር ማህበረሰብ ጋር የሚጣጣም ለገበያ ዝግጁ የሆነ ልማት ከፍተኛ የሆነ ተለዋዋጭነትን የሚያቀርብ የድብልቅ አጠቃቀም የዞን አከላለልን ይመክራል እንዲሁም ለአዳዲስ ህዝባዊ መገልገያዎች እና አስፈላጊ ህዝባዊ ተቋማት እድሎችን ይፈጥራል።




# እየተሳተፉ ይቆዩ

## ቁልፍ ክንውኖች እና የመገኛ መረጃ

እርስዎ በረቂቅ እቅድ ምክረ ኃሳቦቹ **እቅድ ማውጣት ቦርድ የሕዝባዊ ችሎት** ላይ **ሐሙስ፣ ሴፕቴምበር 14፣ 2023 በ6:00 ሰዓት** በ**Montgomery Planning Wheaton Headquarters 2nd floor Auditorium (2425 Reedie Drive, Wheaton, MD 20902)** እንዲሁም **በእቅድ ማውጣት ቦርዱ ድረገጽ በኩል** **ግብረመልስ መስጠት** ይችላሉ። ተጨማሪ የህዝባዊ ችሎት የርቀት መገኛ በ**Takoma Park የማህበረሰብ ማዕከል (7500 Maple Avenue, Takoma Park, MD 20912)** ላይ ይኖራል።

በአካል ወይም በመስመር ላይ **ለመመስከር ለመመዝገብ** ይህንን ድረገጽ ይጠቀሙ። የዕቅድ ማውጣት ቦርድ እና ሰራተኞቹ የሕዝባዊ ችሎት አካል እንዲሆኑ ያበረታታዎታል **http://montgomeryplanning board.org/meetings/signup-to-testify/sign-testify-form/**። የትርጉም እና ማስተርጎም አገልግሎቶች ጥያቄ በማቅረብ ይሰጣሉ። በ**Takoma Park የማህበረሰብ ማዕከል** የህዝባዊ ችሎት የቀጥታ ስርጭትን ለመመስከር ከፈለጉ፣ ተመሳሳይ ሂደትን መከተል እና ለመመስከር መመዝገብ አለብዎት። የTakoma Park የርቀት መገኛን በተመለከተ ላሉ ተጨማሪ ጥያቄዎች እባክዎ **የCity of Takoma Park የማህበረሰብ ልማት ኃላፊ የሆኑት Rosalind Grigsbyን**፣ በ **(301) 891-7205** ላይ ወይም **rosalindg@takomparkmd.gov** ያግኙ።

በተጨማሪም ስለእቅዱ በኢሜል በ **mcp-chair@mncppc.org** በኩል **አስተያየቶችን ማስገባት** ይችላሉ። እነዚህ አስተያየቶች የህዝባዊ ምስክርነት እና የእቅዱ ህዝባዊ መዝገብ አካል ይሆናሉ።

**የሕዝባዊ ችሎት የረቂቅ እቅድ እና አባሪው** በመስመር ላይ ይገኛል(**https://montgomeryplanning.org/planning/communities/downcounty/takoma-park/takoma-park-master-plan/takoma-park-minor-master-plan-amendment/**) ። በተጨማሪም፣ የወረቀት ቅጂዎች በ**Takoma Park Maryland Public Library (7505 New Hampshire Ave, Takoma Park, MD 20912)**፣ **Brigadier General Charles E. McGee Public Library በdowntown Silver Spring (900 Wayne Avenue, Silver Spring, MD 20910) ውስጥ** እና በ**Montgomery Planning's Information Counter ቢሮአችን 2ኛ ፎቅ ላይ በ2425 Reedie Drive** በሚገኘው downtown Wheaton ውስጥ ይገኛሉ።

ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣**Melissa Williams**ን በ**(301) 495-4642** ላይ ወይም በኢሜይል በ**melissa.williams@montgomeryplanning.org** ላይ ያግኙ።

Takoma Park
አነስተኛ የማስተር ፕላን ማሻሻያ
montgomeryplanning.org/tpmma

Montgomery Planning